የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

# 'አይሰስ' በማለት ራሱን የሚጠራው ቡድን በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሰውን አሰቃቂ ጭፍጨፋ ሸንጎ በጥብቅ ያወግዛል!

**ሚያዝያ ፲፪ ፣ ፳፻፯ April 20, 2015**

አይሰስ በማለት ራሱን የሚጠራው ቡድን በሊቢያ ውስጥ በሁለት የተለያዩ ክፍለሀገሮች በያዛቸው ኢትዮጵያውያን ላይ ያለርህራሄና አረመኔያዊ በሆነ መልክ ያካሄደውን ግድያ አለም እንዲያይለት ለማድረግ ያሰራጨውን ቪድዮ የተመለከትነው በከፍተኛ ሃዘንና ቁጭት ነው። ለተጠቂትም ቤተሰቦች ጥናቱን ያገኙ ዘንድ እየተመኘን ይህን ሰብዓዊነት የጎደለውን ተግባር ሸንጎው በጥብቅ ያወግዛል።

ይህ ቡድን እነዚህን ኢትዮጵያውያን አንገታቸውን በመቅላትና በጥይት በመደብደብ ያካሄደው ግድያ በንጹሃንና ምንም ወንጀል ባልሰሩ ነገር ግን ክርስትያንና ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ብቻ መሆኑ የቡድኑ ተግባር መሰረታዊ የእስልምና እምነትን የሚጻረር ብቻ ሳይሆን መሰረታዊ የሰው ልጅ ርህራሄ የጎደለው እንደሆነም ያሳያል። ስለሆነም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ የየትኛውም እምነት ተከታይ ይሁን፣ የፖለቲካ አመለካከት አራማጅ፣ ይህንን ተግባር በአንድ ድምጽ ሊያወግዘው ይገባል። በማንኛውን ኢትዮጵያዊ ላይ የሚፈጸም የግፍ ተግባር በሁላችንም ላይ እንደተፈጸመ የሚቆጠር ነውና በሊቢያ ውስጥ በወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን ግፍ በጋራ እንድናወግዝ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ህዝባችንን በሀይማኖት ከፋፍሎ አብሮ ተባብሮና ተጋግዞ ከመኖር ወደ ጥላቻና ግጭት በዚህ አይነቱ ፈታኝ ተግባር ሊገፋፋት ከቶውንም አይገባም፣ አይቻላቸውምም። ሁሉም ኢትዮጲያውያን ለዘመናት በሚያኮራ የወንድማማችነትና የእህትማማችነት መንፈስ ያዳበርነውን አብሮ የመኖር፣ የመከባበርና የመተሳሰር ባህላችንን ለማንኛውም አይነት ከፋፋይና ጽንፈኛ ሴራ እድል ሳንሰጥ ግንኙነታችንን በማጠናከር፣ ትስስራችንን እያዳበርን ተፋቅሮ መኖር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ሸንጎ ያምናል። ይህን አኩሪ እሴታችንን እንድናዳብረው፣ አኩሪ ታሪካችንን አሁንም እንድንቀጥልበት ሸንጎው ያሳስባል።

በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው አለም የምንገኝ ኢትዮጵያውያንን አንድነትና ጠንካራ ትስስር ለማወክ፣ በሀይማኖት በብሄረስብና በጎሳ በመከፋፈል የእርስ በርስ ሰላም እንዳይኖረን የሚጥሩትን ሁሉ በጋራ እንድንቋቋም ጥሪያችንን በድጋሚ እናሰማለን።

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ብቻ እንዳየነው ኢትዮጵያውያን በነጻነትና ፍትህ ማጣት፣ በኑሮ መማረንና በወደፊት ህይወታቸው ተስፋ በመቁረጥ የተወለዱባትን ወድ ሀገራቸውንና ዘመድ አዝማዳቸውን እየተው በሚያደርጉት ስደት የሚደርስባቸው ጥቃት ከየመን የቦንብ ዝናብ፣ በበሃር መስጠምና ማለቅ፣ በደቡብ አፍሪካ በእሳት ተቃጥሎ መሞትና ሌላ ሌላም ተዘርዝሮ የማያልቅ ስቃይ ዜጎች ሲጋለጡ በምሬት እያየን ነው።

ለብዙ የወገኞቻችን ስደት ዋናው መንስኤ በሀገር ውስጥ በአሸባሪነትና በከፋፋይነት የስልጣን ዘመኑን ለማቆየት የቆረጠው የህወሓት/ወያኔ ፖሊሲወች እና ተግባር መሆኑን ዜጎች ጠንቅቀው የሚያውቁት ነው። ይህን ከፋፋይና አግላይ ስርዓት ማስወገድና በምትኩ ህግና ፍትህ የሰፈነባት፣ ዜጎች መብታቸው ተከብሮ በእኩልነት አብረው የሚኖሩባት ሁሉም ኢትዮጲያውያን የወደፊት ተስፋቸው እንደገና የሚታደስባት በርግጥም ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረት ካልቻልን ስደቱም፣ ጥቃቱም መከራውም ከዚሁ አጥፊ ስርዓት ጋር ጎን ለጎን እንደሚኖር እሙን ነው።

*ሀገራችንና ህዝባችን በከፍተኛ አደጋ ሰር ይገኛሉ፡ በሀገራችን ዙሪያና በተለያዩ ሀገሮች የሚታየው ሀይማኖትንና ጎሳን መሰረት ያደረገ የግጭትና የሽብር አዙሪት ሀገራችንንም እንዳይበክል ሁሉም ባለድርሻ በጋራ የሚመክርበት ብሄራዊ መግባባትና እርቅ ያሰፈልጋል።የኢትዮጵያውያን ዘላቂ ጥቅም እና ሀገራዊ ደህንነት ከጠባብ ፖለቲካ ጥቅም በላይ ነው።*

ሸንጎ

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com